# ወደድንም ጠላንም ካልዘራን አናጭድም!!!

በአንድነት ያበሩ ትውልዶች፤ ለቆሙለት ዓላማ ስኬት በፅናት መታገላቸው የሚያመጣው ውጤት የታወቀ ነው:: ለዚህም ይመስላል ዛሬ ዓለማችን ይህንን መንገድ ተዘንግቶ በተለያየ ፅንፍ የተለያዩ ሃሳቦችን እና ፍላጎቶችን በሰላማዊ መንገድ ማስተናገድ ባለመቻልዋ በሚካሄዱ ትግሎች ንቅናቄ እየጎላ የሚገኘው ይሁንና ለልማትና ዕድገታቸው ቃል የተገባቡ ትውልዶች ግን በቆሙለት ዓላማ የሚያግዳቸውን ማንኛውንም ነገር በፅናት፣ በማስተዋል እና በህብረት ታግለው ተቋቁመው የሚያልፉት።

ሀገራችን ባለፉት ዘመናት ዜጎቿ በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ለማለፋቸው ዋነኛ ምክንያቱ የሚመሩበት ስርዓተ መንግስት የሚያራምደው አቆርቋዥ አስተዳደር መሆኑ እሙን ነው። ታዲያ ያ ዘመን አልፎ በበሳል አመራርና በህዝቦች ያላሰለሰ ሁለገብ ተሳትፎ ትውልዱን ወደ አዲስ የልማትና የዕድገት መንፈስ የሚያሸጋግር የህዳሴ ጉዞ በመፈጠሩ ቢሰሙት የሚያሳምን ቢያዩት የሚያነሳሳ ለውጥ በሃገራችን እየተመዘገበ ይገኛል። ይህ የሆነው ግን በምንም ሳይሆን ልማትን በሚያቀነቅን በጠራ ልማታዊ መስመር በተነደፈ ለውጥ አምጪ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በመታገዙና በጠንካራ የተግባር የለውጥ ሁደት ውስጥ በመግባቱ ጭምር ነው።

መንግስት ሁሉንም ዜጎች ተጠቃሚ ለማድረግ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ከጀመረ ዓመታት ተቆጥረዋል። በዚህ ትግል ውስጥ ደግሞ የህዝብ አንድ የመሆን እንዲሁም ለለውጥ የመታተር ጉዳይ ትኩረት የሚሰጠው ዋነኛ ጉዳይ ነው ምክንያቱም ለዕድገትና ለለውጥ ልዩነቶችን ወደ ጐን በመተው በመቻቻል መንፈስ ለሀገር ልማት በአንድነት የቆመ ህዝብ የሚያመጣው ለውጥ ምን ሊመስል እንደሚችል ከሰለጠኑና የህዝባቸውን ኑሮ ከለወጡ ሀገራት ተሞክሮ ብዙ መማር ይቻላል።

ቀድሞም በሀገራችን የውጭ ወራሪ ኃይልን አንድ ሆኖ በመታገል የተገኘው ታላቅና አኩሪ ድል ለሀገሪቱ ከፍተኛ ክብር የድል አድራጊነት ወኔና መንፈስን ያላበሰ ለዘላለም የሚታወስ የድል አድራጊነት ሃውልት በመሆኑ የዛሬው ትውልድም ከፊቱ እየታገለው ያለውን ድህነት በመታገል አይረሴ አሻራውን በከባድ መስዋዕትነት ማስቀመጥ የሚችለው ጉልበቱን በህብረት ሲጠቀም እንዲሁም ለቆመለት የዕድገትና የለውጥ ዓላማ በፅናት ሲታገል በመሆኑ በአንድነት ዓላማውን ለማሳካት በጠራ አመለካከትና ተግባር የህዳሴው መስመር በፅኑ መሰረት ላይ እንዲገነባ በጽናት መረባረብ ይጠይቃል።

መቼም የተፈጥሮም፣ የማህበረሰቡም ህግ ነውና ወደድንም ጠላንም ካልዘራን አናጭድም ካልሰራን አንቀምስም አንነርስም። የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል ዘመን አልፎ ያልተገላበጠ ያራል ዘመን ላይ መሆናችን እርግጥ ነው። በመሆኑም ሀገራችን ኢትዮጵያ በአላት የሩቅና የቅርብ ጊዜ ታሪኳ በሰላም አፍቃሪነቷ በዓለም እውቅና የተቸራት ሀገር ናት። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ይህንን ለሌሎች ሀገራት የመቻቻል የአብሮነት እንዲሁም በጋራ የማደግ ራዕይ ላልገባቸው ሀገራት ምሳሌ ሊሆን የማይችል በመንግስትና በህዝቦች ያለሰለሰ ጥረት የተፈጠረውን ትልቅ የዕድገታችንን ፀጋ የሚያናጋ ነገር ተፈጥሯል። ለመሆኑ ከዚህ ቀደም የልማትና የመልካም አስተዳደር ችግሮቻችን በተለያየ ወቅት በተከሰቱበት ግዜ አብሮ የመኖር ባህላችንን እንዲሁም የማንነት ጥያቄዎቻችን በሚመለሱበት ሂደት ላይ ያጋጠመን ችግር አለ? ከነበረስ እንዴትስ ልናስተካክለው ቻልን፣ ዛሬስ ያጋጠመንን ልንፈታው የምንችለው ጎራ ለይተን በመካረር ከሆነ ውጤቱ እንደ ሀገር አንድ ላይ ቆሞ በጋራ ለመጓዝ ጥሩ አይሆንም።

የትምክህትና የጠባብነት የኪራይ ሰብሳቢነት እና አክራሪነት የሚባሉት አመለካከቶችና ተግባራት በራሳቸው በመልካም ነገር ላይ መሰረቱን በጣለበት ማህበራዊ መሰረቱ በጠነከረበት ማህበረሰብ ውስጥ የሚነገር በሆነ ኖሮ ራሱ

ህብረተሰቡ የሚጠቅመውን እና የሚጎዳውን በልኩ መመዘን ስለሚችል መልካም ነበር ይሁንና ባልዳበረ መነጋገርና መቻቻል ሰጥቶ መቀበልን ባህሉ ለማድረግ ለሚጥር ማህበረሰብ ግን ከስር ከስር ክትትልና ድጋፍ ያስፈልገዋል። ይህም ማለት ሀገራችን አሁን ካለችበት የለውጥና የዕድገት እንቅስቃሴ መዘወር ውጭ የሚመጡ አደናቃፊ ነገሮች በመሆናቸው በረጋና በሰከነ መንፈስ በማየት መለወጥ እንደሚፈልግ ሀገር ለልማታችን እና ለሰላማችን የሚበጀንን በቅጡ ለይተን መምረጥ ይጠይቀናል።

በሀገራችን የሚገኙ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሁሉ ተቻችለው በመኖር በሀገሪቱ በሚደረጉ የልማት እንቅስቃዎች ውስጥ የበኩላቸውን ዕገዛ ከማድረግ በተጨማሪ በባህላቸው በወግና ስርዓታቸው የሰላምን የአብሮ መኖርና የመፈቃቀርን በእሴቶቻቸው ጠብቀው እየሄዱ ይገኛል በቀጣይም መንግስት፣ ማህብረሰቡ፣ የሃይማኖት እና የትምህርት ተቋማት እንዲሁም ሚድያው ሀገር ወዳድ እና በልዩነት እና በመቻቻል የሚያምኑ ዜገችን ከማፍራት አንጻር በመልካም ሰብዕና በመቅረፅ ለህዳሴ ጉዞው የራሳቸውን አስተዋፅኦቸውን ይበልጥ አጠናክረው ሊቀጥሉበት ይገባል።

የህዝባቸውን የሰቆቃ ኑሮ ለማሻሻልና ሁለንተናዊ ለውጥ ለማምጣት የዕድገት ማነቆ በሆነው ድህነትና ኋላቀርነት ላይ የተረባረቡ ሀገሮች የደረሱበትን ደረጃ እንደ ሀገር እኛም ለመድረስ በየልማት ምዕራፉ የሚየጋጥሙንን ችግሮች በቅጡ በመለየት አስቀድመን በመተንተንና በራዕይ በማመላከት ለሚያጋጥሙ ወቅታዊ ችግሮች አዋጭ አማራጮችን በጥራት በመለየት እና በመንደፍ የጋራ ዋና ዓላማችንን ሳንስት ከህዝብ ጋር እንደ ሃገር እየገጠሙን የሚገኙትን ችግሮች ላይ ግልፅ መግባባት ላይ በመድረስ በጋራ እንደሚፈቱ መተማመን  ይጠይቃል።

ሌላው ዋናው ቁም ነገር አሁን እየታዘብነው ያለው የሁከት፣ የግርግርና የአመፅ እንቅስቃሴ እንዴት በዚህ የዕድገት እንቅስቃሴ መዘውር ውስጥ በገባንበት ሰዓት ሊያጋጥመን ቻለ? የሚለው ጥያቄ ምንም ይሁን ምንም የዚህ አይነት ችግር አንደኛ ደረጃ በነበሩበት ወቅት በደቡብ ኮሪያ፣ በቻይና እና በሌሎችም ሀገራት የገጠሙ ተመሳሳይ ችግሮች በመሆናቸው ሳንደናገጥና ሳንዘናጋ ልማቱ በሂደት የሚፈጥራቸው የህዝብ ጥያቄዎች በመሆናቸው አሁንም ዕድገታችን በቀጠለ ቁጥር ተመሳሳይ ወይንም በባህሪያቸው ለየት ያሉ ስርዓቱን የሚፈታተኑ እንቅስቃሴዎች መኖራቸው የሚጠበቅ በመሆኑ በቀጣይም በህዝብ ውስጥ የተፈጠረውን የለውጥና የዕድገት ስሜት በንቃት በመከታተል እና ለውጡን በቅጡ በመረዳት በተደራጀ አግባብ ምላሽ መስጠት ብቻ ሳይሆን ተመሳሳይ ክስተቶች ዳግም እንዲያጋጥሙ በንቃት መከታተል ሲከሰቱም አምኖ በጥናትና ምርምር ላይ የተመሰረተ የመፍትሄ ሀሳብ ማቅረብ እና በአፋጣኝ እንዲታረሙ ማድረግ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ መሆን አለበት።

በሀገራችን እየተመዘገበ የሚገኘውን የዕድገትና ለውጥ እንቅስቃሴ ምን ማለት እንደሆነ በደንብ መረዳት ይገባል በርካታ ሀገራት ውስጥ ተወዳድረን የምናገኘውን የኢንቨስትመንት ዕድል በአግባቡ በመጠቀም በሂደቱም ኢንቨስትመንቱ የሚቆረቆርበትን አካባቢ ማህበረሰብ ማዕከል በማድረግ በዕድሉ ተሳታፊነቱንና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ይገባናል። ስለዚህ በየአካባቢው የሚገኙ ኢንቨስትመንቶችን ህዝብ እንደራሱ ሀብት በማየት ሊጠብቃቸው ሊንከባከባቸውና ማህበራዊ ከለላ ሊያደርግላቸው ይገባል።

ይህች ሀገር በመንታ መንገድ ላይ የምትገኝ በመሆኑ በጀመረችው የልማትና የዕድገት ጉዞ ውስጥ ይበልጥ ማደግ አለባት። ወደኋላ መመለስ አይገባም በመሆኑም በልማትና መልካም አስተዳደር የህዝብ ጥያቄ ሽፋን እና መነሻ በማድረግ ድብቅ ፖለቲካዊ አጀንዳዎችን በህዝብ ፍላጐት ላይ በመጫን በሁከትና ትርምስ ለማስፈፀም የሚደረገው ጥረት ተገቢነት የሌለውና ህግና ህገመንግስታዊ ስርዓቱን አደጋ ላይ የሚጥል ክስተት በመሆኑ ለቀጣይ ትምህርት

በመውሰድ በየአካባቢው የሚገኝ አመራር ችግሮችን አስቀምጦ ከማጠራቀም ይልቅ በግልፅ በማውጣት ከስር ከስሩ መፍትሄ እንዲሰጠው ማድረግና ድብቅ ዓላማ ያላቸው አካላት ተመሳሳይ ክስተት እንዳይፈጥሩ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠይቃል።

እንደ ህዝብ ቆም ብለን በመተሳሰብና በመቻቻል ከመንግስት ጋር በመቀናጀት ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱ እንዲከበር በማድረግ ስርዓቱን ተከትለን በነደፍናቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እንዲሁም የልማት ዕቅዶች በመታገዝ ለተግባራዊነቱ በመረባረብ በድህነት ላይ ብናብር ጥሩ ይሆናል። የመንግስት ስልጣን የሚታይበትን የኀበጠውን እይታ በማስተካከል ስልጣንን ለህዝብና ለህዝብ አገልግሎት ለመስጠት ብቻ የሚውልበትን መንገድ ተከታትሎ ማጠናከር ይጠይቃል።

ያላበረና አንድ ያልሆነ ህዝብ የሚኖረው እንቅስቃሴ በግል ጥቅም ላይ በሚመሰረት ሰንሰለት ስለሚሆን የራሱን የጥቅም ቡድን በየፈርጁ እንዲደራጅ እድል የሚሰጥ ከመሆኑም በተጨማሪ በነዚህ ክፍሎች ውስጥ የሚፈጠረው የሀይል ሚዛን በሚኖረው ከባድ ተፅዕኖ የሀገርን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል በመሆኑ በቀጣይ እንደ ሀገር በአንድነት ለመንቀሳቀስ የሚያዳግትና የዜጐች በነፃነት የመኖር ጥያቄ በችግር አረንቋ ውስጥ የሚዘፈቅ ይሆናል። ስለዚህ ህብረትና አንድነት በመልካም ሁኔታ ላይ የተመሰረቱ ከሆነ አገር ከጥፋት ህዝብም ከስደት ይድናል በምትኩ ሰላምና ዕድገት በፅኑ መሰረት ላይ እንዲገነባ ምቹ መደላድል ይፈጥራል። የዘራነውን ስለምናጭድ የነገን ትውልድ ዛሬ በጽኑ ማህበራዊ መሰረት ላይ መገንባት ለነገ የቤት ስራ ስለማይሆን ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

ሲሳይ ጥላሁን

26/05/2009 ዓ.ም